ሰኔ1 ቀን 2011
አዲስ አበባ

# 71ኛ መደበኛ የካቢኔ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 71ኛ መደበኛ ስብሰባ በ2012 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ረቂቅ በጀት ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

ለ2012 በጀት ዓመት በፌዴራል መንግስት ለሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን በጀት አፅድቆ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ወቅት ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ እና የፌዴሬሽን ም/ቤት በወሰነው ቀመር መሰረት የፌዴራሉ መንግስት ለክልሎች የሚሰጠውን የድጋፍ በጀት መጠን መወሰን ስለሚኖርበት ከሐምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም በሚፈፀመው በአንድ የበጀት ዓመት ግዜ ውስጥ የፌዴራል መንግስት በጀት ብር 386,954,965,289 (ሶስት መቶ ሰማንያ ስድስት ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሳ አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስድሳ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ብር) እንዲሆን ተወስኗል፡፡

ከዚህ ውስጥ፡-

| | |
|---|---|
| • ለመደበኛ ወጪዎች | 109,468,582,456 |
| • ለካፒታል ወጪዎች | 130,710,876,568 |
| • ለክልሎች የሚሰጥ ድጋፍ | 140,775,506,265 |
| • ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ | 6,000,000,000 |
| ጠቅላላ ድምር | 386,954,965,289 |

እንዲሆን ተመድቧል፡፡

ም/ቤቱ በቀረበው ረቂቅ በጀት ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ተቀብሎ ይፀድቅ ዘንድ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

//